ዶ/ር ማርቲን ሉተር ኪንግ፣ ጁንየር. መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት

Dr. Martin Luther King, Jr. Middle School

# የስነ-ሰው (Humanities ) እና የኮሙዩኒኬሽኖች ማግኔት/ Magnet ፕሮግራም

## ከ6ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ለሚገኙ






13737 Wisteria Drive
Germantown, Maryland 20874
301-353-8080

የማመልከቻ ቅጾች እዚህ ይገኛሉ፡-

www.montgomeryschoolsmd.org/schools/mlkms/ or
www.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/specialprograms

MCPS

Rockville, Maryland

# ፕሮግራም፣ ተማሪዎች፣ እና ሠራተኛ/ኞች

የዶ/ር ማርቲን ሉተር ኪንግ፣ ጁንየር. መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ማዕከል ከላይኛው የሞንትጎመሪ ካውንቲ ክፍል ተስጥኦ የተላበሱ ተማሪዎች ጠንካራ ጥረት የሚጠይቅ ትምህርት ጥናት ፕሮግራም ይሰጣል። ፕሮግራሙ የሚያካትተው በብዙ የትምህርት ዘርፎች ፈርጀ ብዙ የትምህርት ዓይነት፣ ጥናቶችን ነው።

## ♦ ስነ-ሰው /ሂውማኒቲስ/ እና መገናኛ(ኮሙዩኒኬሽን)

የስነ-ሰው (Humanities) እና ኮሙዩኒኬሽን ማእከል ልዩ እና ከበድ-ያለ ውስብስብ /ቻሌንጂንግ/ የመማር እድል ያቀርባል። ይህ ማእከል በጠንካራ ሁለገብ የስነ-ሰው (humanities) ፕሮግራም ዙሪያ ስለተቀረጸ፣ ተማሪዎች በሞንትጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (Montgomery County Public Schools) የጥናቶች/ትምህርቶች ፕሮግራም ውስጥ ቋንቋን የትምህርታዊ ጥያቄዎች ውጤቶችን ለማቅረብና ውጤታማ በሆነ መንገድ መገናኛ ብዙሃን /ሚዲያን/ የመጠቀም ችሎታዎቻቸውን ማሳደግ ላይ ያተኩራል።

በኪንግ የሚድያ ስቱድዮ ውስጥ ተማሪዎች እንደ ፕሮዳክሽን ቡድን አባላት በእጃቸው እየሠሩ የመማር እድል አላቸው። በሂደት-ተኮር፣ ውጤትን መሠረት ያደረገ ስርአተ-ትምህርት ጋር በመስራት፣ ተማሪዎች የትርኢት አቅራቢነት፣ የካሜራ ኦፕሬተርነት፣ አዘጋጅነት፣ የዳሬይክተርነት፣ የድምጽ ኢንጂነር፣ የአርታኢነት፣ እና የግራፊክ አርቲስት ክህሎቶችን ያገኛሉ። ከቴሌቪዥን እውቀት በተጨማሪ፣ ተማሪዎች የህትመት፣ ሬድዮ፣ ቪዲዮ፣ እና ዲጅታል ብዝሃ- ሚዲያ ከመሳሰሉ ሌሎች ሚዲያዎች ላይ ይሰራሉ።

የ ስነ-ዓለም ጥናት (The World Studies) ስርአተ ትምህርት ለስነ-ሰው (humanities) ማእከል ፕሮግራም ማዕቀፍ/ቅርጽ ይሰጣል። ተማሪዎች ለባህላዊ ለውጦች ምክንያቶችን /የሚመሩትን ሃይሎችን/ በመተንተን በተለያዩ ባህሎች መካከል ትስስሮች/ግንኙነቶችን ያጠናሉ/ይፈጥራሉ። ተማሪዎች ወደ እውነተኛው የዓለም ጉዳዮች ችግሮችን የመፍታት ስልት/ዘዴ/ስራዎች የሚመሩትን ስለ ታሪካዊ ክስተቶች/እሴቶች ግንዛቤ ያሳድጋሉ።

ፕሮግራሙ በተጨማሪ ለተማሪዎች በርካታ የጽሁፍ ኮርሶችን እና ምርጥ ለሆኑት የጽሁፍ ውጤቶቻቸው እንዲታተሙ እና እንዲሰራጩ እድሎችን ይሰጣል። ተማሪዎች ስራዎቻቸውን የህትመት ጥራት ለማስያዝ ለማርቀቅ፣ ለማረም፣ እና ለማሳመር ኮምፕዩተሮችን ይጠቀማሉ። የመግለጫ ጽሁፎችን፣ ጨዋታዎችን (plays)፣ እና የህትመት ሚዲያ የመሳሰሉ ስራዎችን በማዘጋጀት የጽሁፍ ችሎታዎቻቸውን በሌሎች ክፍሎች ከተማሯቸው ጋር ያቀናጃሉ።

## ♦ ፋኩልቲ

በፕሮግራሙ ዉስጥ ያሉ መምህራን ባላቸው ጠንካራ የአካደሚክ ችሎታቸው፣ ከፍተኛ የማስተማር ክህሎታቸው፣ እና ከፍተኛ ችሎታ ከተካኑ ተማሪዎች ጋር ለመሥራት ባላቸው ፍላጎት መሰረት የተመረጡ ናቸዉ።

## ♦ ወደ ማእከሉ ለመግባት

ወደ ፕሮግራሙ ለመግባት የሚቻለው በጠንካራ ውድድር ነው። ተወዳዳሪዎችን መገምገሚያ መስፈርት የሚያካትተዉ፣ በተወዳዳሪዎቹ የተጻፉ ጽሑፎች፣ ቀደሞ ያላቸው ውጤቶች፣ የኮርስ ስራ፣ እና የቴስት/የፈተና ውጤቶችን ነው። ተማሪዎች ተከታታይ ቴስቶችን/ፈተናዎችን ኖቬምበር ላይ ያጠናቅቃሉ።

ከሚከተለው የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክለስተሮች ተማሪዎች ዶ/ር ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁንየር መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት (Dr. Martin Luther King, Jr. Middle School) ለሰብአዊ ጥናት ፕሮግራም/Humanities Program ይታደማሉ፡-

- ክላርክበርግ (Clarksburg)
- ዳማስከስ (Damascus)
- ጌትርስበርግ (Gaithersburg)
- ማግሩደር (Magruder)
- ኖርዝዌስት (Northwest)
- ፑልስቪል (Poolesville)
- ኩዊንስ ኦርቻርድ (Quince Orchard)
- ሴኔካ ቫሊ (Seneca Valley)
- ዋትኪንስ ሚል (Watkins Mill)

## ♦ መጓጓዣ/ትራንስፖርት

ከ ዶ/ር ማቲን ሉተር ኪንግ ጁንየር መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት Dr. Martin Luther King, Jr. Middle School ወደ አማካይ ቦታዎች የሚያጓጉዝ ትራንስፖርት ይሰጣል። ለአክቲቪቲ/(ከትምህርት በኋላ) እንቅስቃሴ አውቶብሶች ከሰኞ እስከ ሀሙስ ድረስ ይቀርባሉ።

## ♦ ወደ ዶ/ር ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁንየር መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት Dr. Martin Luther King, Jr. Middle School የሚወስድ አቅጣጫ

- ከአውራ መንገድ ቁጥር 270፣ በስተ ሰሜን፡- ፋዘርኸርሊ ብሉቫርድ/Father Hurley Boulevard ላይ ይውጡ። ዊስቴርያ ድራይቭ/Wisteria Drive ላይ ወደ ቀኝ ይታጠፉ። ወደ ትምህርት ቤቱ ለማቅናት ቀኝዎትን ይያዙ።
- ከአውራ መንገድ ቁጥር I-270፣ በስተደቡብ፡- 15B ላይ ይውጡ። ዊስቲሬያ ድራይቭ/Wisteria Drive ላይ ወደ ቀኝ ይታጠፉ። ት/ቤቱ የሚገኘው በስተቀኝ ነው።

## ♦ የበለጠ መረጃ/ኢንፎርሜሽን

ፎል ላይ በሴንትራል ሎኬሽን /በማዕከል ቦታዎች የወላጅ ስብሰባ ይካሄዳል። ስብሰባው ስለሚካሄድበት ወቅት፣ የመግቢያ አፈጻጸም/ሂደት፣ እና ስለ ፈተና/ቴስት የበለጠ መረጃ ለማግኘት እባክዎ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ድረ-ገጽ ይጎብኙ፡-

- www.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/specialprograms ወይም
- www.montgomeryschoolsmd.org/schools/mlkms

በዶ/ር ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁንየር መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Dr. Martin Luther King, Jr. Middle School) ስለሚካሄደው የሰብአዊ ጥናት ፕሮግራም/Humanities Program ማንም ተጨማሪ መረጃ የሚፈልግ .. ማናገር ይቻላል

Margaret Kay, lead teacher
Dr. Martin Luther King, Jr. Middle School
13737 Wisteria Drive
Germantown, MD 20874
ስልክ፡- 301-353-8080

# የሞንጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) የፀረ-መድሎ መግለጫ
# MCPS Nondiscrimination Statement

የሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) ዘርን፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ የዘር ሃረግ፣ የብሔር ማንነት፣ ኃይማኖት፣ የስደተኝነት ሁኔታ፣ ጾታ፣ ስነ-ጾታ፣ የጾታ ማንነት (gender identity)፣ የጾታ አገላለጽ (gender expression)፣ የጾታዊ ግንኙነት ዝንባሌ/ምርጫ (sexual orientation)፣ የቤተሰብ/የወላጆች የኑሮ ደረጃ/አቋም/ሁኔታ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ እድሜ፣ ድህነት፣ እና የማህበራዊ ኤኮኖሚያዊ አቋም፣ ቋንቋ፣ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳተኝነት፣ በህገመንግስት ጥበቃ የተደረገላቸው ሁኔታዎችን ባህሪያትን ወይም ተዛማጅነት ያላቸውን (affiliations) መሠረት ያደረገ ሕገ-ወጥ አድሎ/መድሎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ በሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነትን፣ ፍትሕ፣ አብሮነት፣ሁሉን አቀፍነትን፣ ለመፍጠርና ለማሳደግ/ለመንከባከብ፤ ሲደረግ የቆየ ትጋትን ይሸረሽራል/ያበላሻል። አድልዎ የሚከተሉትን የተወሰኑ ምሳሌዎችን ያካትታል፡-ጥላቻ፣ ሁከት፣ ደንታቢስነት፣ ወከባ፣ ማስፈራራት፣ ማሸማቀቅ፣ ንቀት፣ ወይም ማጥቃት። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ደምብ/Policy ACA ስለ ጸረ-መድሎ፣ ፍትህ፣ የዳበረ ባህል ይመርምሩ። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ አስፈላጊ/ተፈላጊ መሆኑ(ኗ)ን፣ በተለይም የትምህርት ውጤቶች የሚረጋገጡት በምንም ዓይነት ግለሰብ ባለበት(ባለባት) ምክንያት ወይም ይሆናል ተብሎ የሚገመት ግላዊ ጠባዮች የሚተነበዩ አለመሆናቸውን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በቅድሚያ መወሰድ ስላለባቸው የፍትህ እርምጃዎች የተዛባ አመለካከትን፣ ማረጋገጫ የሌላቸው የማዳላት/ልዩነት አፈጻጸሞችን የሚያስከትሉትን አሉታዊነት፣ የትምህርት እና የሥራ መቀጠር እኩልነትን የሚያሰናክሉ መዋቅራዊ እና ድርጅታዊ አሠራር ደንቃራዎችን በተለይ ያስገነዝባል።

| በMCPS ሰራተኛ* ላይ ስለደረሰ መድሎዎ ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች ለማቅረብ | በMCPS ተማሪዎች ላይ የአድልዎ ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች ካላችሁ* |
|---|---|
| የሰራተኛ ተሳትፎ እና የሥራ ግንኙነት ጽ/ቤት<br>የአፈጻጸም እና የክትትል/የምርመራ መምሪያ<br>Department of Compliance and Investigations<br>850 Hungerford Drive, Room 55<br>Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>OCOO-EmployeeEngagement@mcpsmd.org | የት/ቤት አስተዳደር ጽ/ቤት የአፈጻጸም ክፍል<br>Office of School Administration Compliance Unit<br>850 Hungerford Drive, Room 162<br>Rockville, MD 20850<br>240-740-2540<br>COS-SchoolAdministration@mcpsmd.org |

* ክትትል፣ ቅሬታ/ስሞታ፣ ወይም ስንክልና ላለባቸው ተማሪዎች አመቺ ስፍራ ለመጠየቅ፤ ወደ ልዩ ትምህርት ተቆጣጣሪ ጽ/ቤት፣ የቅሬታ ሰሚና መፍትሔ ሰጪ ን/ክፍል በ ስልክ ቁጥር 240-740-3230 ሊቀርብ/ሊመራ ይችላል። ለሰራተኞች መገልገያዎች ወይም ማሻሻያዎች በሚመለከት የሚቀርቡ ጥያቄዎች ወደ Office of Employee Engagement and Labor Relations, Department of Compliance and Investigations/ የሰራተኛ ተሳትፎ እና የስራ ግንኙነት የአፈጻጸም እና የክትትል (የምርመራዎች) መምርያ፣ ስልክ፡- 240-740-2888 ሊመሩ ይችላሉ። በተጨማሪ፣ አድሎአዊነት ቅሬታዎች ለሌሎች ኤጀንሲዎችም ፋይል ሊደረጉ ይቻላል። እነርሱም፡- the U.S. Equal Employment Opportunity Commission, Baltimore Field Office, City Crescent Bldg, 10 S. Howard Street, Third Floor, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); ወይም U.S. Department of Education, Office for Civil Rights, Lyndon Baines Johnson Dept of Education Bldg., 400 Maryland Avenue, SW, Washington, DC 20202-1100, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, ወይም www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህ ሠነድ ካስፈለገ በሚያቀርቡት ጥያቄ መሠረት ከእንግሊዝኛ በሌሎች ቋንቋዎችና በሌላ አማራጭ ቅርፀት ሊገኝ ይችላል። በአካል ጉዳተኝነት ስለሚኖሩ አሜሪካውያን ደንብ የሞንጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች የህዝብ ኢንፎርሜሽን እና የድረ-ገጽ አገልግሎት ክፍልን በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837, 1-800-735-2258 (ሜሪላንድ ማዞሪያ), ወይም PIO@mcpsmd.org. የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚፈልጉ ግለሰቦች ወይም የንግግር ትርጉም/ምልክት አገልግሎት ለማግኘት የሞንጎመሪ ካውንቲ የህዝብ ት/ቤቶች የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤት በስልክ ቁጥር፡- 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) ወይም MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org መገናኘት ይችላሉ። የሞንጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS)፤ ወጣት ስካውቶችን (ወንድ/ሴት) እና ሌሎችም የሚመለከታቸውን ወጣት ቡድኖችን በእኩል ያስተናግዳቸዋል።

ROCKVILLE, MARYLAND


በመገልገያ እቃዎች/ቁሳቁሶች አስተዳደር መምሪያ ለኮንሶርሽያ ን/ክፍል
የዝንባሌ ምርጫና ማመልከቻ ፕሮግራም አገልግሎት ታተመ
Department of Materials Management for the
Division of Consortia Choice and Application Program Services (DCCAPS)

ትርጉም፡- የቋንቋዎች ትርጉም አገልግሎት ክፍል
Language Assistance Services Unit • Department of Communications

0013.19ct • Editorial ፣ Graphics & Publishing Services • 9/18 • NP